# በኤርትራ ሙዚቃ የምትደንሰዋ ከተማ በወያኔ ትግሬ "ንዓደዪ ንዓደዪ!" አጫፋሪ ትግሬዎች ተጨናንቃለች! መቀሌ!

ጌታቸው ረዳ (Editor Ethiopian Semay)

ወንድሜ ጋዜጠኛ ወንድወሰን ገ/ኪዳን "ኢሳትን ተው በሉት!" በሚል መልዕክቱ ጌትነት እንየው በገጠመው ግጥም እንዲህ ይላል።
"እውነት ቤት ስትሰራ
ውሸት ላግዝ ካለች
ጭቃ ከረገጠች
ምስማር ካቀበለች
ቤቱም አልተሰራ
ዕውነትም አልኖረች"



"The Adeye! Adeye! Group landing in Tigray Mekelle)

የወያኔ ትግራይ ባንዳዎች ከኤርትራ ባንዳዎች የቀዱት "ፌስቲቫል" እያሉ የሚጠሩት ከጫካ ጀምረው "ሥጋ ውድበይ! ሥጋ ወያነ!" በማለት በወያኔ የሚምሉ ለበርካታ አመታት ከገዳሪፍ እስከ መዲኒ ከከሳለ እስከ ካርቱም በሴትኛ አዳሪነት አድረው ለጁኑቮቹ ሚሽላ ቆራጭ ገላቸውን እየሸጡ፤ ያጠራቀሙት ያንገትና እና የጆሮአቸው ሽልማት/ወርቅ/ ለወያኔ ሲያስረክቡ የነበሩትን ሴቶች፤ከዚያም አልፎ ወያኔ በጉቦ ለሱዳን እና ለዓረቦች ለፍትወተ ሥጋ ማርኪያ ሲዳርጋቸው የነበረውን "የሂማን ትራፊኪንግ" ወንጀል አልበቃ ብሎት፤ ጦርነቱ ካለቀ በኋላም ቢሆን "የገቢ ምንጫችን" የሚላቸው እነዚህ ምስኪን የትግራይ ሴቶች"ትግራይ ዓደይ!" የሚሏት ነፃ ከወጣች በኋላም ቢሆን (ተዋጊ ሃይሎቹ ሳይቀሩ) ፤

በወያኔ ትብብር ወደ አሜሪካ እና አውሮጳ በመሸጋገር “የፖለቲካ ጥገኝነት” ተሰጥቷቸው ዛሬ ደግሞ /በዌልፈር/ዕርጥባን/ ወይንም አሜሪካ የሚኖሩ አራዳዎች “ማር ቆረጣ” ብለው በሚጠሩት የሰው ዓይነ ምድር እየጠረጉ “በሆም ኬር” ሥራ ተሰማርተው መከራቸውን እያዩ በስደተኛ ኑሮ ኑሯቸው የሚገፉ እህቶቻችንን ኣእምሮ በመበዝበዝ ፤ የንቃታቸው ዝቅተኛነትን በመጠቀም ዛሬም የወያኔ አገልጋዮች ሆነው ጋዜጠኛው መሐመድ ሰልማን “በኤርትራ ሙዚቃ የምትደንስ ከተማ” ብሎ ወደ ሚጠራት “መቀሌ” ከተማ በትግራይ ፋስቲቫል በዓል ተገኝተው ለመጨፈር ወደ ትግራይ ተጉዘዋል።

“ለማየት እጅግ በሚያስጠላ” ጉብታ የሚያክል ሰው ሰራሽ ፀጉር ተጐንጉነው ውበታቸው እና ወርቃቸውን የሚያሳዩበት ፌስቲቫል መቀሌ ከተማ “ንዓደዬ!” (እልም/ጥርግ ወደ አገሬ!) የሚል ከኤርትራኖች የቀዱት ዘፈን እያስዘፈኑ ሰሞኑን ሲያስጨፍራቸው እየሰነበተ ያለው እነዚህ ሴቶች እህቶቻችን ብቻ ሳይሆን፤ ለስለላ ወደ አሜሪካ፤አውሮጳ እና ካናዳ ያሰማራቸው የወያኔ ወታደራዊ ስለላ አባሎች በፖለቲካ ጥገኝነት አንዲኖሩ የላካቸውንም ጭምር እና በመስፍናዊ እና ፏሺስታዊ ትግራዋይነት ትምክሕት ተወጥረው “ትግራይ ዓደይ! ትግራይ ዓደይ!” የሚሉ “ስጋ መለስ!” ብለው የሚምሉ



እነኚህ “ሳዕኒ መለስ” (የመለስ መጫሚያዎች) የምላቸው የተማሩ ማይማን ምሁራንም በኤርትራኖቹ “ንዓደዬ!” (ወደ አገሬ!”) ሙዚቃ እየታጀበ ቀልባቸውን ስተው ሲጨፍሩ አንድንመለከታቸው “ጌቶቻቸው”

ይህንን ስዕለ ደምፅ ዘርግተውላቸዋል። እኛ ትገሬዎች "ዕብዳን" የምንለው "ኢንሳኒቲውን" የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሰንደቃላማ ወደ ታች ዝቅ ብሎ የወያኔ የባንዳዎቹ ባንዴራ ከፍ ብሎ መቀሌ ከተማ ስትቀበላቸው በቪዲዮው የተቀረጸው ይኼው ይመልከቱ።**The reception ceremony of Tigreans in Diaspora in Mekele Part I [http://youtu.be/BFjYnhqxM5s](http://youtu.be/BFjYnhqxM5s)**

**Easily deceived TPLF Trojan-Horses in action**






ስነ-ስርዓት ኣቀባብላ
ተጋሩ ዲያስፖራ
ኣብ ከተማ መቐለ





## አልቆም-ያለው-የአማራው-ሕዝብ-ሰቆቃ።ዓለም-ዘጠኝ!-ንዓል-አቡክ-አዱኒያ!



**በህዝባቸው አምባ እስክስታ የሚወርዱ እራቃናቸው የወጡ የሕሊና ድኩማን የትግሬ ምሁራን!**

 እውጭ ከታወቀ ከተማ ኗሪ የሆነ አብሮ አደግ ጓደኛዬ ደውሎ “ጐይተኦም” (ጌታቸው) ይለኛል ጥንት በለመደው ስሜ ሲያሞካሸኝ። አየህልኝ መቀሌ ውስጥ  እያደረጉት ያሉትን እነዚህ ማፈሪያዎች አለኝ። አዎ! እየተከታተልኩት ነው፡ አልኩት። አነኚህ “ሥጋ ወድብይ” ብለህ የምታሾፍባቸው “ደቂ ውድበይ” (የድርጅት ልጆች) መንጋጋው በስትሮክ የተቆለፈው “አባይ ወልዱ” “ተጠቀምቲ ንኽትኮኑ” (ተጠቃሚዎች አንድትሆኑ በማሰብ) ከውጭ ለመጣችሁ ዲያስፖራ  ትግሬዎች “መሬት ይሰጣችኋል” ብሎ ሲላቸው በደስታ ብዛት “ለሁለት ደቂቃ” ከተቀመጡበት ተነስተው ሲያንጨበጭቡ አይተህልኛል?! አለኝ። አዎ፡ አልኩት። ለምን ይመስልሃል፤ ደስታውን ያልቻሉት? አለኝ። ምን? አልኩት። ከድሃ የተነጠቀው መሬት ለእነዚህ አሽከሮቹ ሸልሞ፤ለአንድ አመት በባለቤትነት ተመዝግበው በእጃቸው ካቆዩት በኋላ በውድ ዋጋ በጥቁር ገበያ ሸንቁጠው “ተበድረው በክረዲት ካርድ የመጡበትን የትግራይ ፈስቲቫል ዕዳ መክፈያቸው ሊያደርጉት እንደሚችሉ ስላወቁ ነው” አለኝ። “ሱዋኤን ብጡጠን! ” አሃ፤ ሰዋኤን ብጡጠን ነዋ! ጨዋታው አልኩት። አዎ። አለኝ። (ሌባ ጠላ ለመጠጣት ሲል ከጠላ ሻጯ በዝርፊያ ያገኘውን በገዛ ጥጥዋ ተመለሶ ለሷ ሸጦ ጠላዋን ገዝቶ ይጠጣላታል) ማለት ነው።

አዎ ጨዋታው ሁለቱም ወያኔ እና አገልጋዮቹ እርስ በርስ በዝርፍያው ጨዋታ በመሽላለም ያለው”ደግፊኝ ልደግፍህ” ቁማሩን ያውቁበታል። ለዚህ ነበር “ወዲ እነይ ለታይ” (አባይ ወለዱ) መሬት ይሰጣችሗል ሲላቸው ሁለት ደቂቃ ቆመው በደስታ ያንጨበጨቡት። ሽልማት! ከነ ጽጌረዳ አበባ እና ጋሻ መሬት!



እነዚህ ጊልት (ሐፍረት እና ጥፋተኛነት) የማይሰማቸው  የፍየል ዓይን የዋጡ “የትግራይ ምሁራን” መሬት ከድሃው ገበሬ እየተነጠቀ (ምናልባትም  የናቴ አያቶች የነፊታውራሪ ሓጎስና የዘመዶቻቸው የነ ፊታውራሪ ተፈሪ የነበረ ከተነጠቁት ሰፋፊ የከተማ እና የዳርቻ ከተማ መሬቶች አንዱ ሊሆን ይችላል) ሊሰጣቸው ከታቀደው በላይ ከውጭ የመጡ እነዚህ “እራቁታቸው የወጡ” ሃፍረተቢስ ምሁራን ማስተናገጃ ተብሎ የሚወጣው የቡፌ ምግብ /ሪሰፕሽን፤ በማይንድ ኰንትሮል “ወታደራዊ ማርሽ” ነጋሪት እየተጎሰመላቸው አንደ ልዑላን እና ልዕልታት የተደረገላቸው አቀባባል  ወዘተ...ወዘተ.... ስንመለከት ሪሰፕሺኑ እና ጉብኝቱ አገር አቀፍ በሆነው የወያኔ የግል ንብረት “ብሔራዊ” ኢቲ/ቲቪ ለማስተላለፍ የፈጀው ወጪ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፤ እነዚህ ከመላ ዓለም ወደ ትግራይ የጐረፉ  የወያኔ አሽከሮችን ላመስተናገድ የሚወጣው ወጪ “ከአገሪቱ ብሔራዊ ባንክ” (አገሪቱ አንዳለ የወያነ ብትሆንም) “የመንግሥት ባንክ“ (መንግሥት የሚባል ካለ) የሚሸፈነው ከዛች ድሃ አገር አንደሆነ ጥርጥር የለውም። ሁሉም በደጁ! ባንኩም የባንኩ ባለቤትም ያው “ወያኔ እና የወያኔ ልጆቹ!” ናቸው። ዕዳው ያው ከቡና ሽያጭ፤ ከሰሊጥ እና ከአዶላ ወይንም ከትግራይ የወርቅ ማድን ወይንም

ከዕጠን ገቢ አሽከሮቹን ለመጋበዝ ይሽፈናል፤ ማለት ነው። አየ ወያነ “ቃንጫ ዓሶ!” (የማይጥም/የበሰበሰ/የማይበላ አገዳ)

እነዚህ ሐፍረተ ቢስ ወንጀለኞች፤ የዘመዶቻችን ልጆች የድርጅት የፓርቲ ባንዴራ የወያኔ ባንዴራ እና የወያኔ መዝሙር አንደ ብሔራዊ ሰንደቃላማ እና መዝሙር ተደርጐ አንዲቀበሉዋቸው በየትምህርት ቤቶቹ እና ስብሰባው በግድ/በጉልበት አንዲያውለበልቡት እና አንዲዘምሩት ትልቅ ወንጅል እየፈጸሙ ናቸው። ይህ አገርን ባሕር አልባ የአደረገ የባንዳዎች አርማ አንደ ብሔራዊ ሰንደቃላማ በየአደባባዩ እንዲሰቀል በጠመንጃ ጉልበት አስገድደው እንዲውለበለብ ማድረግ “የታሪክ ዓይን የማያፍር” ፈጣጣ ወንጀል ነው ። ወያኔ የወንጀል ትርጉም ባያውቀውም፡ ይህ ወንጀል በህጻናት ዘመዶቻችን እና በሕዝባችን በትግራይ ላይም ሆነ በተቀረው ሕዝባችን “ትልቅ ወንጀል” እየፈጸመ ነው።

ይህ ፋሺስታዊ እና ቻይናዊ ቅድ የድርጅት ባንዴራም ሆነ በግድ እንዲዘምር እየተደረገ ያለው የድርጅት መዝሙር፤ “ያመነም ያላመነም” በግድ አንዲቀበለው የማድረግ የሽፈታነት ባሕሪ ወንጀል በሕግ ለመጠየቅ ለወደፊቱ ትልቅ ክርክር አንደሚያስነሳ እና በግምባር ቀደም “እድሜ ከሰጠን” ተሟጓቹ እኔ እሆናለሁ! ደርግ ያመነም ያለማነም ጨፈጨፈን እያሉ ሲከሱት፤ ተመልሰው ወያኔዎች ዛሬ ያመነም ያላመነም ድርጅታዊ ባንዴራ እና መዝሙር አንዲያውለበልብ እና እንዲዘምር በጠመንጃ አስገድደውታል “ያመነም ያላመነም” ማለት ይኼ ነው! ትንሽ አንኳን አይቀፋቸውም።

<u>የመቀሌ ሕዝብ በጋዜጠኛ ማሕሙድ ሰልማን እይታ</u>

የቆየ ግምገማ። መሐመድ የአዲስ ነገር ጋዜጠኛ የነበረ ነው። “በኤርትራ ሙዚቃ የምትደንስ ከተማ” የሚለው ጽሑፉ ስታነቡ የመቀሌ ተክለ ሰውነት ግልጥ አድርጐ ይገልጸዋል። በ13ኛው ክ/ዘመን የተቆረቆረቺዋ መቀሌ ከተማ እኔም “ሓይካማ” በተባለው የትግርኛ መጽሐፌ ስለ ከተማዋ ምንነት በደርግ እና በሃይለስላሴ ጊዜ በሰፊው ምን ትመስል አንደነበረ የሕዝቡ ጠባይ እና ሕይወት፤ በወያኔ እና በደርግ ጭካኔ ያሳለፈው አሰቃቂ ኑሮ ገልጫለሁ “ሓይካማ” ያልኩትም ለዚህ ነው። መሐመድ ሰልማን ድግሞ መቀሌን በዘመነ ወያኔ ምን አንደምትመስል ነግሮናል።

መቀሌ ዛሬ የወያኔ ባንዳ ትግሬዎች እና በትግራዋይነት ጠባብ ብሄረተኛነት የሰከሩ ባለ ሓብቶች በሥልጣን የባለጉ “የገረብ ቡቡ” ባለቤቶች ወይም “ገረብ ቡቡ ኢፓርታየድ መንድር” ብሎ በሚጠራው

ትግራዋዩ ጋዜጠኛው ዮናስ “አፓርታይድ መንደር” የተከሰተባት የተዋበች ከተማ ሆናለች።

ጋዜጠኛ መሐመድ መቀሌን እንዲህ ይገልጻታል፡

“እውነታው ሌላ ነው፡፤ የመቀሌ ነዋሪ እንደተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል በመልካም አስተዳደር እጦት የሚማረር፤የመናገር ነፃነቱ ከአዲስ አበባ ሲነፃፀር በግማሽ የሚያንስ፤በፍትሕ ዕጦት ሚንገበገብ፤ በአስተዳዳሪዎቹ የብቃት ማነስ የሚያሽሟጥጥ፤በዚህም አልበቃ ብሎት የምሽት የእሳት ዳር ቀልዶችን በመሪዎቹ እየፈጠረ፤እየሳቀ የሚያድር ነው።

....የመቀሌ ሕዝብ በአደባባይ ጭምር “እኛን ለመዋጮና ለምርጫ እንጂ አትፈልፈጉንም፤ረስታችሁናል፤ትዝ አንላችሁም። እያለ ቱባ መሪዎችን ጭምር መውቀስ ጀምሯል። የዕድሜ ባለፀጋ የሆነው መንግሥታችን ደግሞ ምርጫ ሲቃረብ መቀሌን ከመንከባከብ አይቦዝንም። ምን ጐደለ? ምን ይጨመር? የሚሉ የፖለቲካ አሰላፊዎች በመቀሌ ሽር ጉድ ያበዛሉ። ኮብል ስቶን ያነጥፋሉ፤ሕዝብን ለሙዚቃ ጭፈራ ይጋብዙታል፤ የቀድሞውን ዘመን አስከፊነት በፊልም ጭምር ያስኮመኩሙታል፤ በየአደባባዩ፤ በየሲነማ ቤቱ፤እንዲሁም በየመስርያቤቱ። የመቀሌ ሕዘብ ይህችን ጨዋታ አሳምሮ ያውቃታል። የድጋፍ ሰልፍ እየወጣም ቢሆን ያማርራል።

ሆኖም መቀሌ በገዢው ፓርቲ ደስተኛ አትሁን እንጂ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ልቧን ከፍታ የሰጠችም፤የምትሰጥም አትመስልም። በሐገሬው ዘንድ በህወሓት መጨከን በወለዱት መጨከን ተደርጎ ይታያል። ብዙ ታሪካዊ ምክንያቶች ሕዝቡ እንዲያ እንዲሆን አስችለውታል። የህወሓት እና የትግራይ ባንዴራ አንድ ናቸው። ከኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር መሳ የህወሓት መዝሙር በትምህርት ቤቶች ይዘመራል።

ያም ሆኖ ሕዝቡ የከፈልነውን መስዋእትንት ያህል ዲሞክራሲ እና ልማት አላገኘንም። በማለት መንግሥት ላይ የሚሰነዝረው ትችት ከቤተሰባዊ ወግ አልፎ በመጽሐፍ ሳይቀር መውጣት መጀመሩን መቀሌ ወዳጆቼ አጫውተውኛል። “ለዚህ ነበር ልጆቻችን የተሰውት?” የሚል የራሮት ደወል ከየከተማው ማእዝን ዝግ ባለ ደምፅ ይሰማል። በቅርቡም ይህንኑ የሚያስተጋቡ መጽሐፍት መታታም ጀምረዋል። “ጋህዲ” (ደራሲ አስገደ ገ/ሥላሴ) የሚለውን መጽሐፍ መጥቀስ ይቻላል። ይህ መጽሐፍ አራት ክፍሎች ያሉት ሲኾን በየመደብሩ ሞቅ ያለ ገበያን እንዳገኘ ለመታዘብ ችያለሁ።......

"......አዲስ አበባ አንድ ጎረምሳ ወደ አንድ ኪዮስክ ጠጋ ብሎ "እስኪ ሲጋራ ስጠኝ" ይላል። በመቀሌ አንድ ኮበሌ በአቅራቢያው ወደ እሚገኘው አንድ ፎቶ ቤት ሄዶ "እስኪ ናይ ብጻይ መለስ ፎቶ ሀበኒ" (አስኪ የጓድ መለስ ፎቶ ስጠኝ) ይላል። ሁለቱም የጠየቁትን ያገኛሉ።

በመቀሌ የአቶ መለስ ዜናዊ ጉርድ ፎቶ ቤት ከሁለት አመት በፊት በ1.50 ሳንቲም ይሸጥ የነበረ፡ አሁን ኑሮ ተወደደ እና ሦስት ብር ገብቷል። ፎቶ ላይ ያሉት ሰው ግን ለኑሮ ውድነቱ ተጠያቂ አይደረግም። አቶ መለስ በመቀሌ ተወዳጅ እና በሽበሽ ናቸው። የትም ይገኛል። ነዋሪው ሲወጣ ሲገባ ያያቸዋል፤ ያደንቃቸዋል። "ኑርልን አንወድሃለን" ይላቸዋል።
ለምሳሌ መቀሌ ውስጥ የእርሳቸወን ፎቶ ያልለጠፈ ፎቶ ቤት ማግኘት ዘበት ነው። በፎቶ ቤቶቹ እየተገላለጡ እና እየተሽኮረመሙ ፎቶ የተነሱ ውብ ሞዴሎች ፎቶዎቻቸው በፍሬም እየተደረገ ደጅ ይሰቀልላቸዋል። አቶ መለስ በነዚህ ውብ ሞዴሎች ፎቶዎቻቸው በፍሬም እየተደረገ ደጅ ይሰቀልላቸዋል። አቶ መለስ በነዚህ ሞዴሎች መሃል ድንገት ሾልከው ይገባሉ። በቆረጣ!

የመቀሌ ሕዝብ በዓይኑ እና  በመለስ እንዲመጡበት አይሻም።ሰውየው በመቀሌ ተክለ ስብእና ገንብተዋል። ሬስቶራንቶች፤መዝናኛዎች፤ቢሮዎች፤ መኪናዎች የሰውየው ፎቶ በመስቀል ፍቅራቸውን ገልጹላቸዋል። አንድ ቀን "አብርሃ ካስል" ከሚባለው አካባቢ ከሚገኝ "ሞርኒንግ ካፌ" ተብሎ ከሚጠራ አንድ ሸጋ ካፌ ታደምኩ። ዘመናዊ ካፌ ነው። በካፌው በአራቱ ማአዝናት በሚገኙ አራቱም ግድግዳዎች በሚያምር ጥቁር እና ነጭ ቀለም የአራት ታለላቅ የዓለማችን ተፅእኖ ፈጣሪዎች ምስል በውብ ፍሬም ተሰቅሎ ይታያል።  እነዚህ አራቱ ሰዎች እነማን ይመስላችኋል? "ማርቲን ሉተር ኪንግ"፤ "ኔልሰን ማንዴላ"፤ "ማህታማ ጋንዲ"፤ እና አራተኛውን ሰው እናንተው ገምቱ...... የኛው አቶ "መለስ ዜናዊ" ናቸው።

መቀሌ ለአቶ መለስ ክብር ስትል አንድ ዜማም አበርክታለች። "ብርኒሂን" የተባለ።  በርኒሂን የመስቀል ወፍ ማለት ነው (ይህ የእናቴ እህት ስም ነው በነገራችን ላይ። ጌታቸው ረዳ)። አንደ አቶ መለስ ሁሉን ያሟላ ሰው በዘመን አንድ ቢገኝ ነው አንደማለት።" ይላል ጋዜጠኛ መሐመድ ሰልማን "በኤርትራ ሙዚቃ የምትደንስ ከተማ" በሚል ባዲስ ነገር ጋዜጣ በጻፈው የመቀሌ ጉብኝቱ ዘገባ።

"እውነት ቤት ስትሰራ
ውሸት ላግዝ ካለች
ጭቃ ከረገጠች
ምስማር ካቀበለች
ቤቱም አልተሰራ

ዕውነትም አልኖረች” (ግጥም ጌትነት እንየው)

**The reception ceremony of Tigreans in Diaspora in Mekele Part I [http://youtu.be/BFjYnhqxM5s](http://youtu.be/BFjYnhqxM5s)**

ጽሑፌን በዚህ ላሳርግ፡- በኤርትራ ሙዚቃ የምትደንሰዋ ከተማ በወያኔ ትግሬ አጫፋሪ ትግሬዎች ተጨናንቃለች! ዓደዩ ዓደዩ! መቐለ ዓደዩ! መቀሌ!። መቀሌ ምግቡ ቡፌው ቁርጡ ጠጁ፤ዊስኪው ተትረፍርፏል፤ አማራው ከየማሳው በየክፍለሃገሩ እየተፈናቀለ ለጅብ እራት እየተሰጠ “የኢትዮጵያ ረዳት ያለህ! የሕግ ያለህ!” እያለ እርይ! ይላል።መርካቶ ውስጥ ለማኞች ከየምግብ ቤቱ ለምነው በምጽዋት ያገኙትን ርፍራፊ በርሃብ እየተሰቀ ላለው የመንግሥት ሠራተኛ ወስፋት ለማስታገስ “እጇ ሙሉ” ጉርሻ 1.00 ብር፤ እጇ ጎደሎ ደግሞ 50 ሳንቲም ከለማኞች እጅ ይገዛል።ምጽአተ ኣለም! አዲስ አበባ! መቀሌ ግን ለ “ንዓደዩ! ንዓደዩ! በድን” የተዘጋጀ ጉንጉን ቀጤማ እና አበባ “የመቀሌ ጠጅ ጠረኑ መርካቶን አውዶታል! በኢቲቪ ቦምባ እየተቀዳ”! ክፍል ሁለት ይቀጥላል......

ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ) [gtachre@aol.com](mailto:gtachre@aol.com)